# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ብሔራዊ የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ

**ሐምሌ 2006 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ብሔራዊ የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| መግቢያ | 1 |
| ምዕራፍ አንድ፡ ጠቅላላ | 5 |
| 1.1. ሀገራዊ ራዕይ | 5 |
| 1.2. የፖሊሲው ራዕይ | 5 |
| 1.3. ተልዕኮ | 5 |
| 1.4. አጠቃላይ ዓላማ | 5 |
| 1.5. ግቦች | 5 |
| 1.6. መርሆዎች | 6 |
| 1.7. የፖሊሲው ተፈጻሚነት ወሰን | 6 |
| ምዕራፍ ሁለት፡ የፖሊሲው የትኩረት አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች | 7 |
| 2.1. አጠቃላይ የህግ ማዕቀፎች | 7 |
| 2.2. የትኩረት አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች | 8 |
| ምዕራፍ ሦስት፡ የፖሊሲው አፈጻጸም | 13 |
| 3.1. የአፈፃፀም ሥርዓት | 13 |
| 3.2. የባለድርሻ አካላት ሚና | 13 |
| 3.3. የክትትልና ግምገማ ሥርዓት | 19 |
| ማጠቃለያ | 20 |
| የቃላት ፍቺ | 21 |

**መግቢያ**

በአንድ ሀገር ፈጣን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ለማምጣትና ዘላቂ የልማት አቅም ለመገንባት ደህንነቱና ጤንነቱ የተጠበቀና ምርታማ የሆነ አምራች ኃይል መፍጠርና አስተማማኝ የኢንዱስትሪ ሰላም ማስፈን ከወሳኝ ቅድመ ሁኔታዎች አንዱ ነው፡፡ ምቹ የሥራ አካባቢ በመፍጠር የሠራተኛውን ደኅንነትና ጤንነት ለማረጋገጥ አግባብነት ያለው ፖሊሲና ስትራቴጂ መኖር እንደ አንድ ወሳኝ አቅም ይወሰዳል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞ□ራሲ□ዊ ሪፑብሊክ መንግስት በሀገሪቱ ፈጣንና ዘላቂ ልማት ለማረፉቶዓ እንዲቻል አጋዥ የሆነ ፍትሀዊ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋትና በ□ህም ላጁ ተመስርቶ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት መስጠት ቁልአ መሣሪ□ በመሆኑ ትኩረት እንዲሰጠው ተደርጓል፡፡

የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሰብአዊ ቱ□ታ ያለው ሲሆን በሥራ ላይ የተሰማራውን አምራች ኃይል ከጉዳት ይከላከላል፣ ንብረትን ከውድመት ጁ□ብቃል፣ ምቹ የሥራ አካባቢ እንዲፈጠር በማድረግ የሥራ ቅልጥፍና፣ ምርታማነት እና ጥራት በማሳደግ በቱ□ ውስጥ ተ□ቴኬሪ ለመሆን ያስችላል፡፡

በሀገራችን ቀደም ሲል በሥልጣን ላይ የነበሩ የፖለቲካ ሥርዓቶች ያራምዱት የነበረው ፖሊሲ የግሉ ሴክተር በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን ተሳትፎና ሚና ሙሉ በሙሉ የገታ ስለነበር ለኢንዱስትሪዎች መስፋፋት፣ ለሥራ ሁኔታዎች መሻሻልና ለሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ተገቢውን ትኩረት የሰጠ አልነበረም፡፡ በመሆኑም አቅም በፈቀደ መጠን ለመከላከልና ለመ□ታት ይቻሉ የነበሩ የሥራ ላይ አደጋዎችና የጤና ጉዳቶች በሠራተኞች፣ በድርጅትና በሀገር ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሲያስከትሉ ቆይተዋል፡፡

በሀገራችን የሥራ ላይ አደጋዎችን እና በሥራ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ የጤና ችግሮችን በተቀናጀ እና በተደራጀ አግባብ ለመምራት የሚያስችል የሙያ ደህንነትና ጤንነት ፖሊሲ ባለመኖሩ ምክንያት፡-

- የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎቶችን በመከላከል መርህ ላይ ተመስርቶ በሥራ ቦታዎች ለማራመድ የሚያስችል ሥርዓት አልተዘረጋም፡፡

- *የሥራ ላይ አደጋዎችና በሽታዎች በአምራቹ የሰው ኃይል እና በኢኮኖሚው እድገት ላይ እያስከተሉ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ በመለየት ተፅዕኖውን ለመከላከል ወይም ለማስወገድ የሚያስችል ስልት አልተቀየሰም፡፡*
- *ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት አስተባብሮ እና አቀናጅቶ ለመምራት የሚያስችል ሥርዓት ባለመዘርጋቱ የሥራ ላይ አደጋዎችን እና በሽታዎችን የመከላከል ተግባር በትብብርና በቅንጅት አልተመራም፡፡*
- *በሥራ ቦታዎች ስለሚከሰቱ አደጋዎች እና የጤና ችግሮች፣ በእነዚህ ችግሮች ምክንያት የተከሰቱ የሀብት ብክነትና የንብረት ውድመት እንዲሁም የሥራ ላይ አደጋዎችን እና የጤና ጉዳቶችን ለመከላከል እየተወሰዱ ያሉ ዕርምጃዎችን (የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎቶችን) ዓይነት እና ደረጃ፣ በሚወሰደው እርምጃም የተገኘ አወንታዊ ምላሽ የሚመለከት መረጃ አልተደራጀም፡፡*
- *የምርምር እና ሥርፀት ተቋማት ለዘርፉ ትኩረት ሰጥተው ጥናትና ምርምሮች በማድረግ ለሀገሪቱ የኢንዱስትሪ ልማት ማበርከት የሚገባቸውን አስተዋጽኦ አላደረጉም፡፡*

*ከዚህ ጋር በተያያዘ በሀገራችን እየተከሰቱ ያሉ የሥራ ላይ አደጋዎችና የጤና ጉዳቶችን አጠቃላይ ገጽታ የሚያሳዩ ጥናታዊ መረጃዎች ባይኖሩም በዓለም ሥራ ድርጅት ጥናት መሠረት በሥራው ዓለም በየዓመቱ የሚከሰቱ የሥራ ላይ አደጋዎችና በሥራ ምክንያት ከሚመጡ በሽታዎች ኢኮኖሚያዊ ወጪ ከጠቅላላው ዓለም አቀፍ ምርት ገቢ እስከ 4% ድርሻ እንዳለው ያመለክታል፡፡ ስለሆነም፡-*

*ሀ. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 42(2) ለሠራተኞች እንዳጎናጸፈው ደኅንነታቸውና ጤንነታቸው በተረጋገጠበት የሥራ አካባቢዎች የመሥራት መብት ዕውን ለማድረግ፣*

*ለ. ሀገራችን ባፀደቀችው የሙያ ደህንነት፣ ጤንነትና የሥራ አካባቢ አጠባበቅ ዓለም አቀፍ ስምምነት ቁጥር 155 መሠረት ብሔራዊ የሙያ ደህንነት፣ ጤንነትና የሥራ አካባቢ ጥበቃ ፖሊሲን ማዘጋጀት፣ መተግበርና በየጊዜውም ማሻሻል የሚጠበቅባት በመሆኑ፣*

*ሐ. በመከላከል መርህ ላይ □ተመሠረተ ተቋማዊ ቅድመ ዝግጅትና አዳዲስ የአሠራር ዘዴዎችን ሥራ ላይ በማዋል እና የሥራ አካባቢዎችን ምቹ በማድረግ ከአ□ፉ እና ከጤና ጠንቆች □ተ□በቁ እንዲሆኑ የሚያስችል የሙያ ደህንነትና ጤንነት ባሕልን በዘላቂነት ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፣*

መ. የማስፈፀም አቅምን በመገንባት አሣታፊና ጠንካራ የምክክር እና የሕግ አፈጻጸም ሥርፐት በሁሉም ደረጃ በመዘርጋት አስተማማኝ የኢንዱስትሪ ሰላም ለማስፈን፣

ሠ. በሥራ ቦታዎች ለሚከሰቱ አደጋዎችና የጤና ጉዳቶች ተገቢ የሆኑ የህክምና፣ የጉዳት ካሳና የመልሶ ማቋቋም ሥርዓት ለመዘርጋት እንዲቻል ብሔራዊ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ማውጣት አስፈልጓል።

**የፖሊሲው ፀድቆ በሥራ ላይ መዋል:-**

ሀ. በመከላከል መርህ ላይ የተመሠረተ፣ ልማታዊ የሆነ፣ ሽፋኑ ያደገ እና ከኢንዱስትሪ እና ከቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር እየተስፋፋ የሚሄድ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና የተሰጣቸውን የጥራትና የአሠራር ሥርዓቶችን የሚከተል የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት ለመስጠት ያስችላል፡፡

ለ.በየደረጃው ያሉ የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት፣ አሠሪዎች፣ ሠራተኞች እና ማህበሮቻቸው፣ እንዲሁም አግባብነት ያላቸው ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በትብብርና በቅንጅት በማሳተፍ በሠራተኞች ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን እና በኢኮኖሚው ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመከላከል ያስችላል፡፡

ሐ. በሀገር አቀፍ ደረጃ በዘርፉ ያለውን የማስፈጸም አቅም ችግሮች በመፍታት ለፖሊሲና ሕግ ዝግጅት፣ ውጤታማ የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችሉ ስትራቴጂያዊ ጥናቶችን ምርምሮችን ለማካሄድ፣ ወቅታዊ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ለማድረግ ያስችላል፡፡

መ. ባለፉት ዓመታት በአገራችን በሥራ ላይ በዋሉ ፖሊሲዎችና የልማት ዕቅዶች የተመዘገበውን ፈጣን፣ መሠረተ ሰፊና ሕዝቡን በየደረጃው ተጠቃሚ ያደረገ ሀገራዊ ዕድገት ለማስቀጠል፣ የኢንዱስትሪውን ሚና ለማጎልበትና የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ ያግዛል፡፡

በመሆኑም በመከላከል መርህ ላይ የተመሠረተና ሀገራዊ አቅጣጫ የሚሰጥ ብሔራዊ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በሥራ ላይ መዋል በምርትና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የሥራ ላይ አደጋዎችንና በሥራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን በመከላከል ምቹ የሥራ ሁኔታዎችን በመፍጠር፤ በሥራ ላይ አደጋዎችና በሽታዎች ምክንያት የሚፈጠሩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶችን በመቀነስ፣ ብክነትንና ብክለትን በማስወገድ ልማትን በማጎልበት፣ በሥራ ቦታ የአምራቹን የሰው ሃይል መብትና ክብር በማስጠበቅ አለመግባባቶች በሁለትዮሽ እና በሦስትዮሽ ማህበራዊ ምክክር የመፍታት ሥርዓትን እያጠናከረ ምርትና

ምርታማነትን እንዲሁም በገበያ ተወዳዳሪነትን አቅም የሚያጎለብት እና ባጠቃላይም በሀገራችን የሥራ ላይ አደጋዎችን የመከላከል ባህል በሂደት እያሳደገ የኢንዱስትሪ ልማትን እንደሚያፋጥን ይታመናል።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሐምሌ 11 ቀን 2006 ዓ.ም. ባካሄደው 69ኛ መደበኛ ስብሰባ በዚህ ብሔራዊ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ላይ ውይይት እና ማሻሻያዎችን በማድረግ በሥራ ላይ እንዲውል ወስኗል።

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ

### 1.1. ሀገራዊ ራዕይ

በሕዝብ ተሳትፎ እና በሕዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት፤ ማህበራዊ ፍትህ የነገሰባት፤ ከድህነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ያላት ኢትዮጵያን ዕውን ማድረግ።

### 1.2. የፖሊሲው ራዕይ

የሥራ ቦታዎችና ሠራተኞች ከሥራ ላይ አደጋዎች እና በሥራ ምክንያት ከሚመጡ በሽታዎች የተጠበቁ ሆነው ማየት፤

### 1.3. ተልዕኮ

ሀ. በአሠሪና ሠራተኞች መካከል በሁለትዮሽ እንዲሁም መንግሥትን ጨምሮ በሦስትዮሽ ትብብር □ታገዘ ምቹ የሥራ ቦታ መአ□ር፣

ለ. በሥራ ላጁ □ተሰማራውን ምርታማ □ሰ□ ኃጁል ከማናቸውም የሥራ ላይ አደጋዎችና የጤና ጠንቆች መጠበቅ፣

ሐ. ምርታማነትንና የገበያ ተወዳዳሪነትን በማሳደግ የአሠሪውን ትርፋማነት እና የሠራተኛውን የሥራና የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል፣

### 1.4. አጠቃላይ ዓላማ

በሁሉም የሥራ ቦታዎች ቀልጣፋና ውጤታማ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት በመስጠት የሥራ ላይ አደጋ ስጋቶችንና የጤና ጠንቆችን በመከላከልና ከምንጫቸው በመቆጣጠር የሥራ ላይ አደጋዎችን እና በሥራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን በመግታትና ሰብዓዊ ጉዳቶች እንዳይከሰቱ በማድረግ ለሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ልማት አስተዋፅኦ ማድረግ፣

### 1.5. ግቦች

ሀ. መደበኛ ያልሆነውን የሥራ ዘርፍ ጨምሮ በሁሉም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎቶችን ተደራሽ ማድረግ፣

ለ. የሁለትዮሽና የሦስትዮሽ የምክክር ሥርዓት በመዘርጋት የሥራ ላይ አደጋዎችንና የጤና ጉዳቶችን በቅንጅት መከላከል፣

ሐ. ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሠራተኞች (ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ የኤች አይ ቪ ቫይረስ በደማቸው ላለባቸው) ትኩረት የሰጠ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት ማዳረስ፣

መ. ከሥራ ቦታ የሚወጡ በካዮች በአካባቢ ላይ የሚያስከትሉትን ተጽዕኖ በመከላከል አሠሪዎችን፣ ሠራተኞችንና በአጠቃላይም ሕብረተሰቡን ከደህንነትና ጤንነት ጠንቆች መከላከል፣

## 1.6. መርሆዎች

ሀ. የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት የሠራተኞች መሠረታዊ መብት ነው፡፡

ለ. የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት ለሁሉም የሥራ ቦታዎች አስፈላጊ ነው፡፡

ሐ. በሥራ ላይ የሚደርሱ አደጋዎችንና የጤና ጠንቆችን መከላከል ይቻላል፡፡

መ. የሁለትዮሽ እና ሦስትዮሽ ትብብርና ቅንጅት የፖሊሲው ማስፈፀሚያ ቁልፍ መሣሪያዎች ናቸው፡፡

## 1.7. የፖሊሲው ተፈጻሚነት ወሰን

ፖሊሲው በሁሉም የሥራ ቦታዎችና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የፖሊሲው የትኩረት አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች

## 2.1. አጠቃላይ የህግ ማዕቀፎች

ይህ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ከሕገ መንግሥቱ፣ በሥራ ላይ ከዋሉ ፖሊሲዎች እና ከዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንዲሁም በሀገራችን እየተተገበረ ካለው የነፃ ገበያ መር ኢኮኖሚ ሥርዓት ጋር ተጣጥመው በተዘጋጁ የሕግ ማዕቀፎች እንዲመራ የሚደረግ በመሆኑ የሀገሪቱ የሕግ ማዕቀፎች ለፖሊሲው የትኩረት አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች ትግበራ መሠረት ናቸው።

### 2.1.1. ዓላማ

የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት የሚመራባቸው ሕጎች እና ደረጃዎች ፀድቀው ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ የሕግ ተፈፃሚነት ማጠናከር፤

### 2.1.2.. ስትራቴጂዎች

**ሀ.** በመከላከል ላይ ያተኮረ ተደራሽ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የሥራ ሁኔታዎች ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል።

**ለ.** በመስኩ ያሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸው እየተረጋገጠ እንዲፀደቁ ይደረጋል።

**ሐ.** የሥራ ቦታ ደህንነትና ጤንነት ብሔራዊ ሕጎችና ደረጃዎች እየተዘጋጁ እና በየጊዜው እየተሻሻሉ ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።

**መ.** የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ በልማት ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ተካትቶ ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል።

**ሠ.** ለአገልግሎት የተዘጋጁ መሣሪያዎች፣ ጥሬ ዕቃዎች ወይም ኬሚካሎች ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ፣ ጥቅም ላይ ሲውሉ ወይም ሲወገዱ በሠራተኞች እና በአካባቢ ላይ አደጋና የጤና ጉዳት እንዳያስከትሉ ለማድረግ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል።

**ረ.** የሙያ ደህንነትና ጤንነት እና የምክርና የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎቶች በድርጅቶች ተጠናክረው የሚሰጥበት ሥርዓት ይዘረጋል።

**ሰ.** የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት በግሉ ዘርፍ የሚሰጥበት የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል።

**ሸ.** የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል የኤክስቴንሽን አገልግሎት ይደራጃል።

## 2.2. የትኩረት አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች

የፖሊሲውን አጠቃላይ ግቦች ለማሳካት የሚያስችሉ የፖሊሲው የትኩረት አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች የሚከተሉት ናቸው።

**2.2.1. የሥራ ላይ አደጋዎችንና የጤና ጠንቆችን የመከላከል ዝግጁነት ባህል ማሳደግ፣**

**2.2.2. የሥራ ቦታ የጤና አገልግሎቶችን ማሳደግና ተደራሽ ማድረግ፣**

**2.2.3. የጉዳት ካሳ ሥርዓትን ማጠናከር፣**

**2.2.4. የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን ድጋፍ ማጠናከር፣**

### 2.2.1. የሥራ ላይ አደጋዎችንና የጤና ጠንቆችን የመከላከል ዝግጁነት ባህል ማሳደግ

በሥራ ምክንያት የሚከሰቱ አደጋዎችንና የጤና ጠንቆችን በመቆጣጠር ሰብአዊ ጉዳቶች እንዳይከሰቱ በማድረግ የሠራተኞችን ምርታማነት ለማሳደግ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መከላከል በመሆኑ በሥራ ቦታ የመከላከል ባህልን ለማሳደግ የሚያስችሉ ሰፊ የግንዛቤና የአቅም ግንባታ ተግባራትን በማከናወን እና የሚመለከታቸውን አካላት ትብብርና ቅንጅት በማጎልበት እንዲሁም የቁጥጥር ሥርዓቱን በማጠናከር ላይ ያተኮረ እንቅስቃሴ ይደረጋል።

#### 2.2.1.1. ዓላማ

ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ትብብርና ቅንጅት በማጠናከር የሙያ ደህንነትና ጤንነት የማስፈፀም አቅም መገንባት፤

#### 2.2.1.2. ስትራቴጂዎች

**ሀ.** በሙያ ደህንነትና ጤንነት የሠራተኛውን፣ የአሠሪውን እና በአጠቃላይ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ የሚረዱ ተከታታይነት ያላቸው የአሕዝቦት ተግባራት ይከናወናሉ።

**ለ.** መደበኛ ባልሆኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች እና በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማትመከላከል ላይ የተመሠረተ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ግንዛቤና የምክር ድጋፍ ተጠናክሮ ይሰጣል።

**ሐ.** በሙያ ደህንነትና ጤንነት መስክ የሥራ ላይ አደጋ መረጃዎችን ለማደራጀት የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት ተዘርግቶ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል።

መ. በሙያ ደህንነትና ጤንነት ዘርፍ የሰው ኃይል ለማልማት የሚያስችሉ የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች በየደረጃው ይዘረጋሉ፡፡

ሠ. የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎቶችን የአቅም ግንባታ ተግባራት ቀጣይነት ለማረጋገጥ እና የጥናትና ምርምር አቅምን ለማሳደግ ተቋማዊ አደረጃጀት ይጠናከራል፡፡

ረ. ለዘርፉ ዕድገት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

ሰ. የሥራ ቦታ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አመራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

ሸ. የሥራ ላይ አደጋዎችን እና በሥራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን በጋራ ለመከላከል የሚያስችል የሁለትዮሽ፣ የሦስትዮሽ እና የሌሎች የባለድርሻ አካላት ትብብርና ቅንጅት ይጠናከራል፡፡

ቀ. የሥራ ላይ አደጋዎችንና የጤና ጉዳቶችን ከመከላከል አኳያ ከመድን ዋስትና ሰጪ ተቋማት ጋር የትብብርና ቅንጅት ሥርዓት ይፈጠራል፡፡

በ. በዘርፉ የተደራጁ የሙያ ማህበራት ለሙያው ዕድገት የጎላ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ይበረታታሉ፡፡

### 2.2.2. የሥራ ቦታ የጤና አገልግሎቶችን ማሳደግና ተደራሽ ማድረግ

በሥራ ቦታ የሚደርሱ አደጋዎችንና በሽታዎችን መከላከል ቅድሚያ የሚሰጠው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በሥራ ቦታ መከላከልን መሰረት ያደረገ የጤና አገልግሎት በማቋቋም እና በማስፋፋት በሥራ ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ሠራተኞች የሕክምና፣ የድጋፍ እና የእንክብካቤ አገልግሎቶች እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

#### 2.2.2.1. ዓላማ

በሁሉም የሥራ ቦታዎች እንደ ሁኔታው የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ ወይም የጤና አገልግሎት እንዲኖር፣ ያሉትም እንዲጠናከሩ ማድረግ፤

#### 2.2.2.2. ስትራቴጂዎች

ሀ. በሥራ ቦታዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ አገልግሎት እንዲኖር ይደረጋል፡፡

ለ. በሥራ ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ሠራተኞች አፋጣኝ የሕክምና አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

ሐ. በሥራ ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ሠራተኞች አካላዊ እና ስነልቦናዊ ተሃድሶ የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

### 2.2.3. የጉዳት ካሳ ሥርዓትን ማጠናከር

በሥራ ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ሠራተኞች በደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት እንደ ሁኔታው የመስራት ችሎታቸውን ሊያጡ ወይም ሊቀንሱ የሚችሉ በመሆኑ የጉዳቱ መጠን በሕክምና ቦርድ በሚሰጥ ማረጋገጫ መሠረት ከጉዳቱ ዓይነት፣ መጠን እና ጉዳቱ ሊያደርስ ከሚችለው የስነልቦና እና ማህበራዊ ቀውስ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የጉዳት ካሳ የሚያገኙበት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡

#### 2.2.3.1. ዓላማ

ቀልጣፋ እና ፍትሀዊ የጉዳት ካሳ ሥርዓት በመዘርጋት በሥራ ላይ አደጋ እና በሥራ ምክንያት በሚመጣ በሽታ የተጎዱ ሠራተኞች የመብታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤

#### 2.2.3.2. ስትራቴጂዎች

ሀ. ከሥራ ጋር በተያያዘ ለሚደርሱ ጉዳቶችና በሽታዎች ተመጣጣኝ የሆነ የካሳ ክፍያ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

ለ. የካሳ ሥርዓቱ በተለይም ዘላቂ ጉዳት ለደረሰባቸው ሠራተኞች የሰው ሰራሽ አካል እና የአካል ድጋፍ መስጠትን ጨምሮ ውጤታማ የክህሎትና የአካል መልሶ ማቋቋሚያ ሥርዓት መዘርጋትን የሚያካትት ሆኖ ፍትሃዊ ጥቅሞችን የሚያስገኝ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

ሐ. መደበኛ ባልሆነው የኢኮኖሚ ዘርፍ እና በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በሥራ ላይ ለሚደርስ አደጋ ግንዛቤአቸውንና አቅማቸውን በመገንባት የራሳቸውን የጉዳት ካሳ ክፍያ አሸፋፈን ሥርዓት እንዲዘረጉ ይደረጋል፡፡

**መ.** በሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት፣ በሕዝብ ጤና ጥበቃና በማኅበራዊ ዋስትና ሥርዓት መካከል የተጠናከረ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡

### 2.2.4. የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን ድጋፍ ማጠናከር

በሥራ ምክንያት የሚከሰቱ አደጋዎች እና በሽታዎች ከአካላዊ ጥንካሬ፣ ከተፈጥሯዊ ሁኔታ እና በሽታን ከመቋቋም አቅም ጋር በተያያዘ በተለይ በሴቶች፣ በወጣቶች፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው እና የኤች አይ ቪ እና ኤድስ ቫይረስ በደማቸው ያለባቸው ሠራተኞች ወ.ዘ.ተ. ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ ተገቢ የመከላከያ እርምጃ እና የህግ ጥበቃ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ከሥራ ቦታ የሚወጡ በካዮች በአካባቢ ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ በካዮቹ ወደ አካባቢ ከመለቀቃቸው በፊት የማከም እና ተገቢውን ጥንቃቄ ለመውሰድ የሚያስፈልጉ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ማድረግ ሁለንተናዊ ጠቀሜታ አለው፡፡

#### 2.2.4.1. ዓላማ

**ሀ.** ሴቶች፣ ወጣቶች እና የአካል ጉዳት ያለባቸው ሠራተኞች የሥራ ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ እና የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ ደረጃ በደረጃ እንዲወገድ ማድረግ፤

**ለ.** የሥራ ቦታ ኤች አይ ቪ እና ኤድስ ምላሽ ከሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት ጋር ተቀናጅቶ እንዲካሄድ ማድረግ፤

**ሐ.** የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎቶች የአካባቢ ጥበቃን እና ከብክለትና ከብክነት የፀዳ የአሰራር ዘዴን ታሳቢ ያደረጉ እንዲሆኑ ማድረግ፤

#### 2.2.4.2. ስትራቴጂዎች

**ሀ.** የሥራ ቦታዎች ለሴት እና ለነፍሰ ጡር ሠራተኞች የተመቻቹ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

**ለ.** ወጣት ሠራተኞች ለአካላቸው እና ለጤናቸው አደገኛ እና ጎጂ በሆኑ ሥራዎች እንዳይሰማሩ ለመከላከል የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፡፡

**ሐ.** አካል ጉዳተኞች ከአካላዊ አቋማቸውና የሙያ ብቃታቸው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የሥራ ሁኔታ እንዲመቻችላቸው ይደረጋል፡፡

**መ.** በሥራ ቦታዎች ኤች አይ ቪ እና ኤድስን የመከላከል፣ □መቆ□□ር፣ የድጋፍ እና እንክብካቤ አገልግሎቶች ከሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት ጋር ተቀናጅተው እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

ሠ. የኤች አይ ቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው ሠራተኞች የጤና መረጃ በሚስጥር እንዲያዝ፣ በሥራ ቦታ አድልዎና መገለል እንዳይደርስባቸው ይደረጋል፡፡

ረ. ከሥራ ቦታ የሚወጡ በካዮች በአካባቢ ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ተገቢው የጥንቃቄ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል፡፡

ሰ. የአመራረት ሂደት የሀብት ብክነትን እና የአካባቢን ብክለት የማያስከትል እንዲሆን ይደረጋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት
# የፖሊሲው አፈጻጸም

## 3.1. የአፈፃፀም ሥርዓት

ፖሊሲውን ተግባራዊ በማድረግ የሀገሪቱን ዕድገት ለማፋጠንና ኅብረተሰቡን ይበልጥ ተጠቃሚ ለማድረግ የተጀመረውን የኢንዱስትሪ እድገት ጉዞ የሚያሳልጥ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ሥርዓት ይዘረጋል። የአፈፃፀም ሥርዓቱ በዘርፉ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ ጥናትና ምርምሮችን የማካሄድ፣ የሴክተር ፖሊሲዎችንና ሕጎችን የማዘጋጀት፣ የአፈጻጸም ክፍተቶችን በመለየት የማሻሻያ እርምጃዎችን የመውሰድ እና የማስፈፀም አቅም የመገንባት ሃላፊነት ይኖረዋል።

በፖሊሲው ላይ ተመስርቶ የዘርፉን ልማት አጠቃላይ አቅጣጫ የሚያመለክት □ዕቅት ማክቀአ በማ□ቶ□ት በፌደራልና በክልል ደረጃ በሥራ ላይ እንዲውል የማስተባበርና የመከታተል ኃላፊነት ያለው ብሔራዊ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ካውንስል በመንግሥት ይቋቋማል።

ካውንስሉ በተለጹም በሙያ ደህንነትና ጤንነት ጉዳዮች ላይ ጥናት እንዲደረግ የሚያማክር፣ የፖሊሲውን አፈፃፀም ተከታትሎ ሪፖርት የሚያቀርብና ቴክኒካዊ ምክር የሚሰጥ ከተለያዩ ዘርፎች የተውጣጣ ባለሙያዎችን የያዘ የቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል።

### 3.2. የባለድርሻ አካላት ሚና

#### 3.2.1. መንግሥት

ሀ. የሚመለከታቸውን የፌዴራልና የክልል አስተዳደር መዋቅሮችን፣ በየደረጃው ያሉ አስፈጻሚ አካላትን እና የአሠሪና የሠራተኛ ማኅበራትን በማስተባበርና በማሳተፍ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ሥርዓት እንዲዘረጋና ተፈጻሚ እንዲደረግ መሪ ሚና ይጫወታል።

ለ. ለሀገሪቱ ፈጣን ልማት አጋዥ የሆኑ፣መልካም አስተዳደርን የሚያሰፍኑና ለብሔራዊ ጥቅም ፋይዳ ያላቸውን ዓለም አቀፍ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ስምምነቶች ያፀድቃል።

ሐ. ከአሠሪዎችና ከሠራተኛ ማህበራት ወኪሎች ጋር በመመካከር ከህገ መንግሥቱ፣ ከዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ ከሀገራዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች እና ከተስማሚ የቴክኖሎጂ ሽግግር ጋር የተገናዘቡና በጥናት የተደገፉ ፖሊሲዎችና የሕግ ማዕቀፎች ያወጣል፣ ተፈፃሚነታቸውንም ያረጋግጣል።

መ. ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች እንዲሁም መንግስታት ጋር ለብሔራዊ የሙያ □ህንነትና ጤንነት ልማት የሚውሉ የቴክኒክ ትብብር ስምምነቶችን ያደርጋል።

ሠ. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር የሙያ ደህንነትና ጤንነትን በተመለከተ ለኢንዱስትሪ የግንባታ ፕላኖች፣ ለአሠራር ሂደቶች፣ ለጥሬ ዕቃዎች፣ ለሥራ

መሣሪያዎችና ለአገልግሎቶች የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ያዘጋጃል፣ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።

ረ. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር አደገኛና በጤና ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ የሥራ ሂደቶች፣ ጥሬ ዕቃዎችና መሣሪያዎች ስለሚከለከሉበት፤ በአሠራራቸው ላይ ቁ□ብ ስለሚ□ረግበትና በልዩ ፈቃድ ሥራ ላይ ስለሚውሉበት ሁኔታ ይወስናል።

ሰ. ለሙያ ደህንነትና ጤንነት ልማት በየደረጃው እያደገ የሚሄድ ሀብት ይመድባል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል።

ሸ. ደረጃውን የጠበቀ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ሥርዓተ-ትምህርት ያዘጋጃል፤ የዘርፉን የማስፈፀም አቅም ይገነባል፣ በየደረጃው የሠለጠነ የሰው ኃይል እንዲሟላ □□ርፉል።

ቀ. ትኩረት በሚሹ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጉዳዮች ዙሪያ ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት ጥናትና ምርምር እንቲካሄት □□ርፉል።

በ. በሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ የግሉ ሴክተር ተሳትፎና የሲቪክ/የሙያ ማህበራት ሚና ደረጃ በደረጃ እንዲያድግ ይደግፋል፣ ያበረታታል።

ተ. የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅን በተመለከተ የሚነደፉ የልማት ዕቅዶች ሥርዓተ ፆታን፣ የአካባቢ ጥበቃን፣ ኤች አይ ቪ እና ኤድስንና ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑ ሠራተኞች ትኩረት የሰጡና ያካተቱ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

ቸ. የሙያ ደህንነትና ጤንነትን የተመለከቱ መረጃዎችን ለሁሉም ባለድርሻ አካላት፣ ለሕዝብና አግባብነት ላላቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል ብቃት ያለው የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት ያቋቁማል፤ የመረጃዎቹንም ደረጃ ይወስናል፣ ተግባራዊም ያደርጋል።

ኀ. ሞትን ጨምሮ ከሥራ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ በሽታዎችንና የአካል ጉዳቶችን ለመካስ የሚያስችል የኃላፊነትና የካሳ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል።

ነ. ከፍተኛ ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳት የሚያስከትሉ የሥራ ላይ አደጋዎችን ለመከላከልና ለመ□ታት የሚያስችል የአደጋ ቅድመ ማስጠንቀቂያ እና ምላሽ ሥርዓት ጄ□ረፉል፣ ተፈፃሚነቱንም ያረጋግጣል።

## 3.2.2. አሠሪና የአሠሪ ማህበራት

ሀ. የሥራ አካባቢዎች ምቹ፣ ጤናማና ከአደጋ የተጠበቀ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ።

ለ. የኢንዱስትሪ ግንባታ ፕላኖች፣ ለሥራ የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎች፣ የመገልገያ መሣሪያዎችና ማሽነሪዎች፣ የሥራ ሂደቶችና የአሠራር ዘዴዎች በሠራተኞች ላጁ አደጋ የማያስከትሉና አካባቢን የማይበክሉ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ።

ሐ. ተገቢነት ያላቸውን፣ ደረጃቸውን የጠበቁ የሥራ ልብሶችና የነፍስ ወከፍ የጉዳት መከላከያ መሳሪያዎችን ለሁሉም ሠራተኞች በነፃ ያቀርባል፤ ስለ አጠቃቀሙም ሥልጠናና መመሪያ ይሰጣል፣ ጁቆ□□ራል።

መ. በሥራ አካባቢ ለሚከሰት የሥራ ላይ አደጋ ወይም ሕመም ተጐጂዎች አፋጣኝ የህክምና እርዳታ እንዲያቐኙና አቅም በፈቀደ መጠን የተሐድሶ ፕሮግራም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋሉ።

ሠ. ፖሊሲውን እና ፖሊሲውን ለማስፈጸም የሚወጡ የህግ ማዕቀፎችን መሰረት በማድረግ በድርጅት □ስዓ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ የሥራ መመሪያ ያዘጋጃሉ፤ ከሠራተኞች ማህበር ወይም ከሠራተኛ ወኪሎች ጋር በመመካከር የመመሪያውን ይዘት በየጊዜው ያሻሽላሉ፣ ተ□ነሚ □□ርፉሉ።

ረ. ፖሊሲውን ለማስፈጸም የሚያስችሉ እርምጃዎች ይወስዳሉ፣ እርምጃዎቹም ከማኔጅመንት አካላት እና ከሠራተኞች ማህበር ወይም ከሠራተኞች የተውጣጣ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ኮሚቴ ማቋቋም፣ የአደጋ ተከላካይ ሠራተኛ መመደብ፣ ዓመታዊ ዕቅድ ማዘጋጀትና ለተግባራዊነቱ የሚያስፈልግ ሃብት መመደብን ይጨምራል።

ሰ. በሥራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችና አደጋዎች የሚመዘገቡበትን አሠራር ጁ□ረፉሉ፣ ለሚመለከተው አካል ወቅታዊ ሪፖርት መደረጉን ያረጋግጣሉ።

ሸ. ሠራተኞች በመከላከል መርህ ላጁ □ተመሠረተ □ሙ□ □ህንነትና ጤንነት ባህል እንዲያዳብሩ አስፈላጊውን ዓ ረት □□ርፉል።

ቀ. በድርጅት ደረጃ የሚሰጥ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት በሠራተኞች መካከል በብሔረሰብ፣ በ□ታ፣ በአካል ጉዳት፣ በሃይማኖት□ በ□ ለቲካ አመለካከት፣ የኤች አይ ቪ ቫይረስ በደም ውስጥ በመኖሩ ምክንያት ልዩነትና መድልዎ እንዳይኖር ያደርጋል።

### 3.2.3. ሠራተኞችና የሠራተኞች ማህበራት

ሀ. የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅን በየደረጃው ለመዘርጋትና ምቹ የሥራ ሁኔታ ለመፍጠር ከአሠሪዎችና ከመንግሥት ጋር በቅንጅትና በትብብር ይሠራሉ።

**ለ.** የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅን በተመለከተ ፖሊሲዎችና የሕግ ማዕቀፎች ሲዘጋጁና ሲሻሻሉ ይሳተፋሉ፣ በአባሎቻቸው ዘንድ ግንዛቤ እንዲጨበጥ ያደርጋሉ፣ በሥራ ላይ □□ላሉ።

**ሐ.** በሥራ ሂ□ት ወይም ከሥራ ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ አደጋዎችና ከሥራ ጋር በተ□□□ □ጤና ጠንቆች ሲከሰቱ ሁኔታዎቹን ለቅርብ □ሥራ ኃላፊ እና ለአሠሪ □ሳ□ቃሉ።

**መ.** በግል የተሰጡ የአደጋ መከላከያ እና የደህንነት መጠበቂያ መሣሪያዎችንና የሥራ መገልገያ ቁሳቁሶችን በጥንቃቄ ይይዛሉ፣ በአግባቡ ይገለገላሉ።

**ሠ.** በድርጅት፣ በሴክተር እና በብሔራዊ ደረጃ በሚቋቋሙ የሁለትዮሽና የሦስትዮሽ የድርድርና የምክክር መድረኮች ላይ ይሳተፋሉ።

**ረ.** በድርጅት ደረጃ በሚቋቋሙ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴዎች ውስጥ በንቃት ይሳተፋሉ።

**ሰ.** በሥራ ቦታ በሚከሰት አደጋ ሳቢያ የጤና ጉዳት፣ የህይወትና የንብረት ጥፋት እንዳይደርስ አስፈላጊውን ዕርዳታ □□ርፋሉ፣ ጉዳቱን ለመቀነስ በሚወሰዱ እርምጃዎች ይሳተፋሉ።

**ሸ.** የሙያ ደህንነትንና ጤንነትን ለማስ□በቅ፣ ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የሠራተኞችንና የማህበራት ግንዛቤ እና ተሳትፎ ለማሳደግ የአቅም ግንባታ ተ□ባራትን ያከናውናሉ።

**ቀ.** በ□□ረጸ□ □ሚካሄ□ □ሙ□ □ህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ፕሮግራሞች ለሴቶች፣ ለወጣቶችና ለአካል ጉዳተኞች እንዲሁም ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ላለባቸው ሠራተኞች ትኩረት እንዲሰጡ □□ርፋሉ፣ ይ□□ኛሉ።

## 3.2.4. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት

**ሀ.** በሙያ ደህንነትና ጤንነት መስክ የሙያ ደረጃዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ያደርጋሉ።

**ለ.** በሙያ ደህንነትና ጤንነት መስክ በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል ያፈራሉ።

**ሐ.** በሙያ ደህንነትና ጤንነት መስክ ለተሰማሩ ባለሙያዎች ከቴክኖሎጂ ሽግግር ጋር የተጣጣመ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠናዎች ይሰጣሉ።

**መ.** ምቹና ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ አካባቢ በመፍጠር ረገድ የቴክኒክ ምክርና የድጋፍ አገልግሎት ይሰጣሉ።

**ሠ.** ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት ለባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል።

### 3.2.5. የከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት

**ሀ**. በሙያ ደህንነትና ጤንነት መስክ የሰለጠነ የሰው ኃይል ያፈራሉ፡፡

**ለ**. በሙያ ደህንነትና ጤንነት መስክ ለተሰማሩ ባለሙያዎች አግባብነት ያለውን የሙያ ማሻሻያ ሥልጠናዎች ይሰጣሉ፡፡

**ሐ**. በሥራ ላይ የሚከሰቱ አደጋዎችን በመከላከልና ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ የአደጋ ስጋቶችን በማስወገድ ላይ ያተኮሩ ጥናቶችና ምርምሮች ያካሂዳሉ፣ የፖሊሲ ሃሳብ ያመነጫሉ፡፡

**መ**. የሙያ ደህንነትና ጤንነት ልማት ለመደገፍ የሚያስችል የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥርዓት እንዲዘረጋና ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

**ሠ**. በሥራ ላይ አደጋና ጉዳት መንስኤ ናቸው ተብለው በሚገመቱ ቁሶች ላይ አስፈላጊውን ሳይንሳዊ ምርመራ ያካሂዳሉ፣ ውጤቱንና መወሰድ የሚገባውን ቀጣይ እርምጃ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋሉ፡፡

**ረ**. ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት ለባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣሉ፡፡

### 3.2.6. የማህበራዊ ዋስትናና የመድን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት

**ሀ**. አሠሪዎች የሥራ ላይ አደጋን እና በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታን የመከላከልና ጉዳትን የመቋቋም አቅም መፍጠር እንዲችሉ የመድን ዋስትና እንዲኖራቸው ያበረታታሉ፣ የአገልግሎቱን ሽፋን ያሳድጋሉ፡፡

**ለ**. የመድን ዋስትና በተገባባቸው ድርጅቶች ውስጥ መከላከልን ቅድሚያ ትኩረት ያደረገ የህክምናና የካሣ ክፍያ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

**ሐ**. የዋስትና ሽፋን ባላቸው ድርጅቶች ውስጥ የደረሱ የሥራ ላይ አደጋዎችና የጤና ጉዳቶች ዓይነት፣ ብዛትና በዚህ ሳቢያ የተከሰቱ ኢኮኖሚያዊ ወጪዎችን ይመዘግባሉ፣ መረጃዎችን ለሚመለከታቸው ያሰራጫሉ፡፡

**መ**. በብሔራዊ፣ በሴክተርና በድርጅት ደረጃ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ዓላማን ለማራመት የሚዘጋጁ ፕሮግራሞችን (ትምህርታዊ መትረኮች፣ የፓናል ውይይቶች፣ ኮንፍረንሶች፣ ብሔራዊ በዓላት) ይደግፋሉ፡፡

### 3.2.7. ዲዛይን አውጪዎች፣ አምራቾች፣ አስመጪዎችና አከፋፋዮች

በሥራ ሂደት ጥቅም ላይ የሚውሉ የማምረቻ መሣሪያዎች፣ ምርቶችና ጥሬ ዕቃዎች ዲዛይን □ሚ□□ርግ፣ □ሚ□መርት፣ □ሚ□ስመጣና የሚያከፋፍል ማናቸውም ሰው ወይም ትርፀ ት፡-

ሀ. መሣሪ□□· □ጁም ምርቱ □ጁም ዓሬ ክቃ□· ሥራ ላይ ሲ□·ል አደጋ የማያደርስና የጤና ጉዳት የማያስከትል መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡

ለ. መሣሪያው ወይም ምርቱ ወይም ጥሬ ዕቃው አደጋና የጤና ስጋት የማያስከትል ስለመሆኑ ፍተሻና ምርመራ ያካሂዳሉ፤ □ጁም እንዲካሄድ ያደርጋሉ፡፡

ሐ. መሣሪያውን ወይም ምርቱን ወይም ጥሬ ዕቃውን የተመለከቱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት የጥንቃቄ መመሪያዎችና የቁስ ደህንነት መረጃዎች በመስጠት መሣሪያዎች፣ ምርቶች ወይም ጥሬ ዕቃዎች በሥራ ላይ ጉዳት ሳያስከትሉ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ለማድረግ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፡፡

መ. ጭነት በማጓጓዝ ሥራ ላይ የተሰማሩ አደገኛና የጤና ጠንቅ ባህርይ ያላቸውን ቁሳቁሶች በሚጭኑ፣ በሚያጓጉዙና በሚያራግፉ ላጁ በዓለም አቀፍና በብሔራዊ ደረጃዎች የተደነገጉ የደህንነትና የጤንነት አጠባበቅ መመሪያዎችን ተፈፃሚ □□ርፉሉ፡፡

ሠ. መሣሪያዎች፣ ጥሬ ዕቃዎችና ምርቶች ተገቢ የደህንነትና ጤንነት መረጃዎችን የያዙ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፣ ለሚመለከታቸው አካላትም ያሰራጫሉ፡፡

### 3.2.8. የሲቪክና የሙያ ማህበራት

ሀ. በየደረጃው የሚካሄዱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ፕሮግራሞችን □በረታታሉ፣ □□□ሉ፡፡

ለ. የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅን የተመለከቱ የግንዛቤ ማሳደጊያ ፕሮግራሞችን □□ፉጻሉ፣ □ሠራተኛ□·ንና የሕብረተሰቡን □ሌአ ቲ ባህል ለማሳደግ ጁሠራሉ፡፡

ሐ. በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ የሙያ ደህንነትና ጤንነት የመረጃ ሥርዓት እንዲዘረጋ ይተባበራሉ፣ ያግዛሉ፡፡

መ. በዘርፉ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያከናውናሉ፡፡

ሠ. በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ያሉ ምርጥ ተሞክሮዎች እንዲስፋፉ ያደርጋሉ፡፡

ረ. በሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ የበጎ ፈቃደኛነት ባህል እንዲዳብር □በረታታሉ፡፡

### 3.3. የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

የፖሊሲውን አፈፃፀም ደረጃ በደረጃ ለመከታተልና ለመቋቋም፣ □ቅታዊ የሪፖርት ልውውጥ አሠራርን ለማጠናከርና ከባለድርሻ አካላት የሚሰጡ ግብረ መልሶችን በግብአትነት ለመጠቀም የሚያስችል ቋሚ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

የክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ ብሔራዊ የሙያ ደህንነትና ጤንነት መረጃ ሥርዓት መዘርጋትን፣ በመረጃ ላይ በመመስረት የፖሊሲውን እና የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎቶችን፣ የሥራ ላይ አደጋዎችን እና የጤና ችግሮችን በመከላከል እና በመቀነስ ረገድ እንዲሁም የሥራ ሁኔታዎችን በማሻሻል ለምርታማነት ማደግ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ በመገምገም ፋይዳቸውን ከሚያስከትሉት ወጪ ጋር የሚያነጻጽር ጥናት ማካሄድን ይጨምራል፡፡

በክትትልና ግምገማው ውጤት መሠረት ፖሊሲውን ለመከለስና የፕሮግራም አፈጻጸሞችን ለማሻሻል የሚያስችሉ መረጃዎች፣ ሪፖርቶች፣ ጥናቶች እና ምክረ ሀሳቦች በየጊዜው ለመንግሥት እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡

ፖሊሲው በሥራ ላይ ስለመዋሉ የመከታተል፤ የብሔራዊ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ሥርዓቱን ለማሻሻል የሚወሰዱ እርምጃዎች ውጤታማነት የመገምገም እና ለሚመለከታቸው አካላት ተገቢውን መረጃ የመስጠትና የማሳወቅ ኃላፊነት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው፡፡ ለዚህም ማኅበራዊ አጋሮችን እና ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ የፖሊሲውን አፈጻጸም የተመለከተ ግምገማ በተወሰነ ጊዜ በመደበኛ ፕሮግራም ይካሄዳል፡፡
ከድርጅት ጀምሮ እስከ ብሔራዊ ደረጃ ባሉ እርከኖች የክትትልና ግምገማ ስርዓት ይዘረጋል፡፡ የፖሊሲው አፈፃፀም ከሥራ ላይ አደጋ መረጃዎች፣ በሥራ ምክንያት ከሚመጡ በሽታዎች፣ ከህክምና፣ ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ወ.ዘ.ተ. ጋር ተያይዞ የደረሱ ጉዳቶችን ያካተቱ ተጨባጭ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ ክትትልና ግምገማ ይካሄዳል፡፡

## 4. ማጠቃለያ

ብሔራዊ ፖሊሲው በሥራ ቦታ የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ መወሰድ ስለሚገባቸው የመከላከያ እርምጃዎች፤ እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች ያሉባቸው ክፍተቶች ተለይተው መስተካከል ስለሚገባቸው የሥራ ሁኔታዎች፤ ከኢንዱስትሪ ዕድገትና ልማት ጋር ተያይዞ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡና ሥራ ላይ የሚውሉ ቴክኖሎጂዎች ስለሚያስከትሉት አሉታዊ

ተፅዕኖዎች ወ.ዘ.ተ. የመከላከያ እርምጃዎች ለመውሰድና ምቹ የሥራ ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችል ሕገመንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገለት ፖሊሲ ነው፡፡

በአጠቃላይ ፖሊሲው የሥራ ቦታ ማህበረሰብ ከሥራ ጋር ተያይዞ ከሚመጡ ደህንነትና ጤንነት ችግሮችና አደጋዎች እንዲጠበቅ፤ በኢንዱስትሪ አካባቢ ነዋሪ የሆነው ህብረተሰብ በኢንዱስትሪው ምክንያት ከሚከሰት ከአካባቢ ብክለት ተጠብቆና ልማታዊ ተሳትፎው ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞቹ እንዲረጋገጡለት እንዲሁም ደረጃውን የጠበቀ ምርት ወይም አገልግሎት ለማቅረብ የሚያስችል መርሆዎችን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ፖሊሲው እነዚህን መሠረታዊ ጉዳዮች ታሳቢ ያደረገ በመሆኑ በኢንዱስትሪዎች የሚመረቱ ምርቶችና የሚሰጡ አገልግሎቶች ከብክለት የተጠበቁና ሰብአዊ መብቶችን ያረጋገጡ ይሆናሉ፡፡ ይህንን መርህ ያሟላ የኢንዱስትሪ ግንኙነት ሰላማዊ፣ በውይይትና በምክክር ላይ የተመሠረተ ስለሚሆን ጥራቱን የጠበቀ ምርት በማመረት ወይም አገልግሎት በመስጠት ምርታማና በገበያ ተወዳዳሪ ከመሆኑም በላይ በሀገሪቱ የኢንዱስትሪ ልማት የሚረጋገጥበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

ይህ ፖሊሲ በሥራ ቦታዎች ስለሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠቃላይ ሀገራዊ አቅጣጫ የሚሰጥ ሲሆን፣ ይህንኑ መሠረት በማድረግ በየኢንዱስትሪው ዘርፍ ተግባራዊ የሚደረጉ ሴክተር አቀፍ ፖሊሲዎችና የማስፈፀሚያ ስልቶች ይዘረጋሉ፡፡ እንደዚሁም የሥራ ቦታዎች ወይም ድርጅቶች ከየሴክተሮቻቸው የፖሊሲ ማዕቀፍ የተቀዳ የሥራ ቦታ የሰፍቲ ፖሊሲ/ደንብ እና የማስፀሚያ ስልቶች ነድፈው ተግባራዊ እንዲያድርጉ ይጠበቃል፡፡

## 5. የቃላት ፍቺ

*"**የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ**"* ማለት በመከላከል መርህ ላይ የተመሰረተ፣ የሥራ ቦታዎች ምቹ፣ ጤናማና ከአደጋ የተጠበቁ እንዲሆኑ ለማድረግ፣ ጤናማ አምራች ዜጋ ለመፍጠርና የሥራ ውጤትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችል የተደራጀ፣ በሥርዓት የሚመራና በቅንጅት የሚፈጸም የልማት እንቅስቃሴ ነው፡፡

*"**የሥራ ላይ አደጋ**"* **(Occupational Accident)** ማለት ማንኛውም ሠራተኛ ሥራውን በማከናወን ላይ ሳለ ወይም ከሥራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ከራሱ ውጭ በሆነ ምክንያት ወይም ሥራውን ለማከናወን ባደረገው ጥረት ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ

ማንኛውም ክፍል ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴ ላይ ወይም በንብረት ላይ በድንገት የደረሰ ጉዳት ነው፡፡ ይህም ፍቺ "***የሙያ ደኅንነት***" የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ የያዘ ነው፡፡

***"በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ"*** ማለት ሠራተኛው ከሚሰራው ሥራ ዓይነት ወይም ከሚያከነውነው ሥራ አካበቢ የተነሳ በሽታው ከተከሰተበት ዕለት አስቀድሞ በነበረ የተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለፊዚካል፣ ኬሚካል፣ ባዮሎጂካልና ኢርጎኖሚካል ጠንቆች በመጋለጥ የሚደርስ አካላዊና አዕምሮአዊ ጉዳት ነው፡፡ ይህም ፍቺ "***የሙያ ጤንነት***" የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ የያዘ ነው፡፡

"***የአካል ጉዳት"*** ማለት የመስራት ችሎታ መቀነስን ወይም ማጣትን በሚያስከትል ሁኔታ በሥራ ላይ የሚደረስ ጉዳት ነው፡፡

"***ወጣት ሠራተኛ"*** ማለት አግባብ ባለው ሕግ በሚወሰነው የዕድሜ ወሰን ውስጥ የሚካተት እና ልዩ ጥበቃ የሚያስፈልገው ሠራተኛ ማለት ነው፡፡

"**ምቹ ሥራ**" **(Decent Work)** ማለት ምርታማ፣ በቂ ገቢ የሚያስገኝ፣ ከአደጋና የጤና ጉዳት የተጠበቀ፣ የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎት እንዲሻሻል የሚያግዝ፣ አመላካከትን በነጻነት የመግለጽ መብትን የሚያከብር፣ ጥቅሞችንና ፍላጎቶችን በሚመለከት በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ የተደራጀና የላቀ ተሳትፎን የሚፈቅድና ለሴቶችና ለወጣቶች እኩል እድልና ተሳትፎ የሚያጎናጽፍ ሥራ ነው፡፡

" ***ብሔራዊ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ሥርዓት***" ማለት ብሔራዊ ፖሊሲውንና በሥራ ላይ ያሉ ህጎችን፣ ሀገር አቀፍ የሙያ ደህንነትና ጤንነት እቅድን፣ በየደረጃው የተቋቋሙ የሶስትዮሽ የምክክር አካላትን፣ የህግ አሰፈጻሚ መዋቅሮችን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን የተቀናጀ አሠራር የሚያስተባብር የመሰረት ልማት ማዕቀፍ ነው፡፡

"***የሥራ ቦታ***" ማለት ማንኛውም ሠራተኛ ለሥራ የሚገኝበት ወይም በሥራ ምክንያት የሚሄድበት እና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በአሠሪው ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ሥፍራ ሲሆን ድርጅቱ በመደበው መጓጓዣ ከመኖሪያ ቤታቸው ወደ ሥራ ቦታ ወይም ከሥራ ቦታ ወደ ቤታቸው የሚጓጓዙበትንም ይጨምራል፡፡

"***አሠሪ"*** ማለት ሠራተኞችን ቀጥሮ የሚያሰራ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ነው፡፡

«***ሠራተኛ”*** ማለት ተቀጥረው የሚሰሩ ዜጎችን ሁሉ የሚያጠቃለል ሲሆን የመንግስት ሠራተኞችን እና መደበኛ ባልሆነው የኢኮኖሚ ዘርፍ የተሰማሩትንም ይጨምራል፡፡

«***ድርጅት***» ማለት ምርት ለማምረት፣ አገልግሎት ለመስጠት ወይም ለሌላ ሕጋዊ ዓላማ የተቋቋመ ተቋም ሲሆን ይህም በመንግሥት፣ በግል፣ በማህበር፣ ራስን በራስ ለማስተዳደር የተቋቋሙትን ሁሉ ይጨምራል፡፡

«***ጠንቅ*»*** **(Hazard)** ማለት ማንኛውም በንክኪ፣በትንፋሽ ወይም በሌሎች የመጋለጫ መንገዶች ሳቢያ የህመም ወይም የአካል ጉዳት የማድረስ ወይም የሥራ አካባቢን የመበከል ውጤት ያለው ንጥረ ነገር፣ ቁስ፣ መሳሪያ ወይም ስነ ህይወታዊ ተውሳክ ነው፡፡

***“ማህበራዊ ምክክር”*****(Social Dialogue)** ማለት በመንግሥት፣ በሠራተኞች እና በአሠሪዎች ተወካዮች መካከል ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን በሚመለከቱ የጋራ ጉዳዮች ላይ የሚደረግ ማንኛውንም ድርድር፣ ምክክር ወይም የመረጃ ልውውጥ ነው፡፡ ምክክሩ በአሠሪ እና በሠራተኞች ተወካዮች መካከል ሲካሄድ ***“የሁለትዮሽ ምክክር”***ሲባል ምክክሩ መንግሥትን የሚጨምር ሲሆን ***“የሶስትዮሽ ምክክር”*** ይሆናል፡፡

***“አሕዝቦት”*** **(Popularization)** ማለት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የግንዛቤ ማሳደጊያ ሥራ መሥራት ማለት ነው፡፡